# ጅል አትሁን!



የአያትህን ታሪክ ብትመረምረው፣
ፈረንጅ ቱርክና አረብ ማታለል ያልቻለው፣
አንጠርጥሮ አንባቢ አራት ዓይን ነበረው።

አንተን የልጅ ልጁን ምንድን ቢያፈዝህ ነው፣
የሚያንከረፍፍህ ሱሳም ቁማርተኛው?

ብልሆች አባቶች ተረት ሲተርቱ በተንከረፈፈ፣
ሁሌ ተንዘላዝሎ ወላጁን ዘመዱን እጅግ ባሳፈረ፣
"ጅልን ተወለደ ያነቀው ፀደቀ!" ይሉን ነበረ።

ጅል አትሁን!

ዓለም በዘር ካስማ በኃይል ተወጥራ፣
እውነት ማተብ ፍትህ እንጦሮጦስ ገብታ፣
አንተ "ሰው ነኝ" የሚል ድስኩር ብታናፋ!
በኢትዮጵያ ገንዘህ ብታስበላ አማራ፣
ጅቡ አንተንም አይመር ጨለማው ሲመጣ።

ጅል አትሁን!

የዘር ቆርጣሚ አውሬ አላማ እንዲገባህ፣
በአምሳ ዓመቱ ልምድህ ስንት ይጨመርልህ?

ጅል አትሁን!

በአባይ ጎርፍ ግድብ እየሸነገሉህ፣
በ"ሱሷ" ኢትዮጵያ "እንግእ እ...እ"ያጫወቱህ፣
እስከ መቼ ጮርቃ እንደ ጨቅላ እያዩህ፣
ተምድር እስክጠፋ ዘርህን ይቆርጥሙህ?

ጅል አትሁን!

ያለ ክንድ ድርድር ሲመጣ ያየኸው፣
ያለ ጉልበት እርቅም ሲሰፍን የሰማኸው፣
በየትኛው ዓለም የትኛው አገር ነው?

ጅል አትሁን!

የዘር አገዛዝን የምታስወግደው፣
እየለመንክ ሳይሆን "እንቀጹን ሰርዘው"፣
ጉዳይ የሚያስፈጥም ስልጣን ስትይዝ ነው።

ጅል አትሁን!

የኢትዮጵያን አንድነት የምትጠብቀው፣
ተለማምጠህ ሳይሆን እግር ልሰህ የሰው፣
በደንብ ተደራጅተህ ክንድን ስታሳየው፣
ማን የገነባውን ማን አፍራሽ ስትለው።

ጅል አትሁን!

በላይነህ አባተ (abatebelai@yahoo.com)
ሐምሌ ሁለት ሺ አስራ አራት ዓ.ም.